ችው በአገራችን በእስፔን ውስጥ ዘወትር እየተከለሰ የሚዘፈነው ቀጥሎ ያለው የማይረሳ ግጥም እንዲህ ይላል ።

“ድል ነስቶ ሲመለስ ከእንግሊዝ አገር ፤
ሴቶች በእልልታ ከፍ ባለ ክብር ፤

እየተቀበሉ የሠገዱለት ፤
ወይዛዝርት ሁሉ ያገለገሉት ።

ምን ጊዜም አልነበር በምድር ላይ ከቶ ፤
ጉበዝ ደፋር ጀግና እንዳላንቺሎቶ” ።

ይህንና ሌላም እዚህ ላይ ያልተጻፈውን ግጥም እጅግ በሚያስደስት ዜማ እየዘፈነች ላንቺሎቶን ስለጠንካራው የጀብዱ ሞያውና ስለ ፍቅራዊነቱ ታሞግሰው ነበር ። ከዚያን ጊዜ ወዲህ ይህ የፈረሰኞች ሕግ እያደር እየተስፋፋና እየተዘረጋ በብዙ ልዩ ልዩ የዓለም ክፍሎች ተዳረሰ ። በየአገሩ ከተነሱትም ዙዋሪ ፈረሰኞች ውስጥ ከዚህ ቀጥሎ ስማቸው የተጠቀሰው ፈረሰኞች መታወስ ይገባቸዋል ። ጉበዙ የጋውላው አማዲስ ከነልጆቹና እስከነ የልጅ ልጆቹ እስከ አምስተኛው ትውልድ ድረስ ስመጥሩነቱ እንደተወራረሰ ዘልቋል ። ጀግናው የኢርካኒያው ፊልቺማርቴና ምን ጊዜም በበቂነት ያልተመሰገነው ቲራንቴ ነጩ ፤ የሁሉም መደምደሚያ የማይሸነፈው ቆፍጣናው የግሪኩ ዶን ቤሊያኒጂስ የነዚህ የጉበዝ አውራዎች ታሪክ በዘመናችን የተሰማና የታወቀ ነው ለማለት እንችላለን ። ስለዚህ አሁን ለርስዎ ለወንድሜ ለማስረዳት የምፈቅደው ዙዋሪ ፈረሰኛ ማለት በነዚህ እላይ በጠቀስኳቸው ጀግኖች ሲከናወን የኖረ ድፍረትንና ቆራጥነትን ፤ መከራ ቻይነትን የሚጠይቅ ጠንካራ ተግባር መሆኑን ነው ።

ቅድም እንደተናገርኩት ምንም እንኳ እኔ እስከዛሬ ድረስ እድለቢስነት ባይለየኝና ባይቀናኝም ተግባሬ እንዲሆን መርጬ የያዝኩት ይህንኑ አሁን የማከናውነውን የፈረሰኛነት ተግባር ስለሆነ ፤ በዚህ ምክንያት ተገፋፍቼ በነዚህ በረሀዎችና ውድማ በሆኑት ቀበሌዎች አጋጣሚዬን ለመፈለግ እየተዘዋወርኩ ደካማዎችን ለማገዝና እርዳታም የሚፈልጉትን ለመርዳት ክንዴንና መላ ሰውነቴን ኃይለኛ ለሆነው አደጋ እያጋፈጥኩ በእድሌ ላይ



እንዲደርስ የታዘዘውን ሳልማረርና ሳልበሳጭ ለመቀበል በቁርጠኛ ልብ የተዘጋጀሁ ሁኜ በመገኘቴ ለዚህ ግዴታ መልካም አፈጻጸም የጦር መሣሪያ መያዝ የሚገባኝ ሆነ ።

በዚህ በዶን ኪሾት ንግግርና አስተያየት ብርሃን መንገደኞቹ በሙሉ ያላንዳች መጠራጠር እብድነቱን ለማመን ስለቻሉ በመጀመሪያ ጊዜ ተገናኝተው ሁኔታውን የሚመለከቱት ሰዎች እንደሚሆኑት ሁሉ እነሱም ግራ ገብቷቸው ቆይተው በመጨረሻው የእብደቱን ዓይነት ከተረዱት በኋላ ባነጋገሩና ባኳኋኑ እጅግ ተደነቁበት ።

ቪባልዶ የሚባለውም ሰው በተፈጥሮው ብልጥና ቀልደኛ ስለነበረ ወደ መቃብሩ ሥፍራ ለመድረስ ጥቂት ይቀረዋል የተባለውን መንገድ እስኪጨርሱ ድረስ አጫዋች ወሬ አግኝተው የሚሰማቸውን ድካም ለማቃለል በማሰብ ዶን ኪሾት ያንን የተዘበራረቀ ታሪኩን ድውር እንዲተረትር በማለት እንዲህ ሲል ቆስቁሶ አነሳሳው ።

“የተከበሩ ዘዋሪ ፈረሰኛ ሆይ እንደሚመስለኝ ይህ መርጠው የያዙት ተግባር ያፈጻጸሙ ሕግ በምድር ገጽ ላይ ከሚገኙት ጥብቅ ሕግጋቶችና ግዳጆች ይበልጥ የጠበቀ ይመስለኛል ። በበኩሌ እንደማውቀው የቼርቶዚን ገዳም ሕግጋት እንኳ እስከዚህ ድረስ የሚጠብቅ አይመስለኝም ።

ዶን ኪሾትም እንዲህ ሲል መለሰ ፤ “ከነሱም ሕግጋት ይበልጥ የጠበቀና የከረረ ሊሆን ይችላል ፤ እንዲሁም ደግሞ ይህ ተግባር ለዓለም ሰላም አጠባበቅ አስፈላጊነቱና ጠቃሚነቱ እጅግ ከፍ ያለ መሆኑን ለመጠራጠር አልቃጣም ። እውነቱን ለመናገር ከሆነ ከሻምበል አዛዡ የተቀበለውን ትእዛዝ በሚገባ የፈጸመ ወታደር ከዚያው ከአዛዡ የሚያንስ አይደለም ። ይህንንም የምልበት ምክንያት ፤ የገዳም መነኮሳት በረጋ ሰላምና በእረፍት ሥፍራ ተቀምጠው አምላክ ምሕረቱን በምድር ላይ እንዲያወርድላቸው በጾምና በጸሎት ሲለምኑ እነሱ በጸሎትና በጾም ለምነው የሚያስገኙትን ምሕረትና ሰላም እኛ ወታደሮችና ዙዋሪ ፈረሰኞች ደግሞ በክንዶቻችን ኃይልና በጉራዴያችን ስለት

እንደነበረ ፤ የጂሮስስቶሞስም ፍቅር የቱን ያህል የጋለ እንደነበረ ፤ አንተም የወዳጅህን ፍቅር በማጥበቅ ረገድ ያሳየኸው መታመንና ቁም ነገራምነት የቱን ያህል የተቀደሰ እንደሆነ በቀላሉ ለመረዳት ችለናል ። ስለዚህ የፍቅር ማዕበል ያናወጸው አዕምሮአቸው የገመተውንና ትክክለኛም መስሎ የታያቸውን በመከተል ያለልጓም የሚጋልቡት አንዳንድ የከንፍ ሰዎች የሚሰጡትን ትእዛዝ መፈጸም በውነቱ ታላቅ ጅልነት ነው ።

"ትናንትና የጂሮስስቶሞስን መሞትና በዚሁ ቀበሌ መቀበር ሰምተን ለወሬው በመጓጓት ብቻ ሳይሆን በኃዘን ስሜት ተገፋፍተን ወሬውን ከእረኞች ስንሰማ እጅግ አድርጐ ያሳዘነን ታሪክ እቦታው ላይ ተገኝተን ሁኔታውን በዓይናችን ለማየት ስንል የመንገዳችንን አቅጣጫ ትተን ወደዚህ መጣን ። ይህን በማሰብ ወዳጄ አምብሮጂዎ ሆይ ፤ በዚህ በጐ ስሜታችንና እንዲሁም የሚቻለን ቢሆን ወዳጅና ዘመዶቹን ለማጽናናትና የሀዘኑ ተካፋዮች ለመሆን ሳደረብን ጽኑ ፍላጐት ካሣ ይሆነን ዘንድ በበኩሌ አጥብቄ የምለምንህ መልካም ፈቃድህ ሆኖ እነዚህን ድርሰቶች እንዳታቃጥላቸውና እኔም ከነሱ መካከል ጥቂቶቹን መርጬ እንድወስድ እሺ እንድትለኝ ነው" ። ካለ በኋላ የእረኛውን መልስና የተስማሚነት ፈቃድ ሳይጠብቅ እጁን ሰደደና ቅርብ ከሚገኙት ድርሰቶች አንደኛውን ጥራዝ አንስቶ ወሰደ ። አምብሮጂዎም ይህን አወሳሰድ ተመለከተና እንዲህ አለ ።

"ወንድሜ ሆይ ፤ ለፍላጐትህ የሚጠቅምህ ከሆነ ያንኑ ያነሳኸውን እንድትወስድ ፈቅጄልሀለሁ ፤ ዳሩ ግን የተቀሩት እንዳላቃጥላቸው በማለት ያቀረብህልኝን ልመና እንድፈጽም ማሰብህ ከንቱ ምኞት ነው" ፤ አለው ።

ቪባልዶም ድርሰቱ የሚለውን ለማወቅ በጣም ቸኩሎ ነበርና አንዱን ገጽ ገልጦ ሲያነብ "የብስጭት እንጉርጉሮ" የሚለውን አርእስት ተመለከተ ። አብሮጂዎም ይህን እንደሰማ እንዲህ ሲል አስረዳ ። "ጌቶቼ ሆይ ፤ በዚህ አርእስት ሥር የተጻፈው ግጥም ሟቹ ወዳጄ በመጨረሻው ጊዜ የጻፈው ነው ። ዕድለቢስነቱ ወደየትኛው አደጋ ላይ እንደጣለው እሱ ላይ ተጽፎ



ታገኙታላችሁ ። ካለ በኋላ ሁሉም ለመስማት እንዲችሉ ድምጽህን ከፍ አድርግና አንብብላቸው ፤ መቸም ጉድጓዱ ተቆፍሮ እስኪያልቅ ድረስ በቂ ጊዜ ስላላችሁ እሱን እየሰማችሁ ለመጠበቅ ትችላላችሁ አላቸው ።

ቪባልዶም "መልካም ፈቃዱ ነው አለና ለማንበብ ተዘጋጀ "እነዚያም ዙሪያውን ከብበው ንግግሩን የሚያዳምጡት ሰዎች የሁሉም ፍላጐት አንድ ዓይነት ነበርና በድርሰቱ ላይ የተገጠመውን ሃሳብ ለመስማት ሲሉ አንባቢውን ከመካከል አድርገው ክባቸውን አጥብበው ቆሙ ። አንባቢውም ድምጹን ከፍ አድርጎ ቀጥሎ ያለውን ግጥም ማሰማት ጀመረ ።

